# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 106 ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ: "የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:" የሚል ነው።**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ "እምቢ ለመብቴ!!!" ብቻ ነው**

## ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የእሁዱን የምርጫ ተውኔት አወገዘ፤ ለኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሃይሎችም ጥሪ አቀረበ

ንቅናቄው ግንቦት 17 ቀን "ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ "እምቢ ለመብቴ!!!" ብቻ ነው" በሚል ርእስ ባወጣው በዚሁ መግለጫ፥ "በምርጫ ስም ሰሞኑን ወያኔ የፈጸመው አስነዋሪ ድርጊት ባለፉት 19 ዓመታት ሲያሳየን የኖረው የንቀትና የውርደት ስልጠናው ከፍተኛው መገለጫ ነው" ብሏል:: ወያኔ ምርጫውን ሙሉ በሙሉ አሸንፌያለሁ ማለቱም እታመናለሁ ብሎ ሳይሆን 'እስቲ የምትሆኑትን አያለሁ' የሚል በእብሪት የተሞላ ንቀቱን ለማሳየት እንደሆነም ገልጿል።

"በምርጫ ስም ወያኔ ሰሞኑን የፈጸመው ነውር ..እምቢ ለዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ በሚል እልህ ከሁሉም የሃገራችን የዴሞክራሲ ሃይሎች ጋር ተባብረን ወያኔን ከማስወገድ ውጭ በሃገራችን ዴሞክራሲን ማስፈን እንደማንችል አመላክቶናል" ካለ በኋላ "የግንቦት 7 የወቅቱ የትግል ጥሪ:- 'የጋራ ውርደት እንዲያከትም፣ በጋራ እብሪተኞችን እምቢ እንበል!!!' ነው" በማለት መግለጫውን አጠቃሏል። (የመግለጫው ሙሉ ቃል በገጽ 4 ቀርቧል)

## በርካታ የተቃዋሚ ፓርቲዎችና የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን እንዲሁም የአሜሪካ መንግስትን የኢትዮጵያን የምርጫ ውጤት ውድቅ አደረጉ

በኦባማ አስተዳደር የአፍሪካ ጉዳይ ሃላፊ ሚስተር ጆኒ ካርሰን ለተወካዮች ምክር ቤት አባላት ባደረጉት ንግግር ባለፈው እሁድ በኢትዮጵያ የተካሄደው የምርጫ ተውኔት ዓለማቀፍ የምርጫ መስፈርቶችን አላሟላም ሲሉ ገልጸዋል።

ሚ/ር ካርሰን የዘረኛውና አምባገነናዊው መለስ አገዛዝ "ላለፉት አሥራ ስምንት ወራት የተሰጠዉን ድምጽ ሁሉ ለመዉሰድ ግልጽ የሆኑ እርምጃዎች ሲወስድ ነበር» ካሉ በኋላ "ኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ተቋማትን በተጠናከረ ሁኔታ አሻሽላ መገንባት እንዳለባት እናምናለን"፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ምንም አይነት ጫና ሳይደረግበት በነጻነት ያሻውን የሚመርጥበት ሁኔታ መመቻቸት እንደሚገባውም ባንክሮ ገልጸዋል፡፡

ከ19 ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ተፈናጥጦ የሚገኘው የአምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ በሰባዊ መብቶች ላይ የሚያደርገውን ጫና ዋሽንግተን ጠንቅቃ እንደምታውቅ የሮይተርስ ዘገባ ያመለክታል። እንደሮይተርስ ዘገባ በኢሃዴግ መንግስት ላይ የአሜሪካን መንግስት እንዲህ አይነት መግለጫ ሲያወጣ በታሪኩ የመጀመሪያ መሆኑንና የኦባማ አስተዳደር በኢትዮጵያ ላይ የሚወስደው ቀጣይ ርምጃ ምን ሊሆን እንደሚችል የታወቀ ነገር የለም ብሏል።

ከዚሁ ዜና ጋር በተያያዘ አምባገነኑ መለስ የአውሮፓን የምርጫ ታዛቢ ቡድን ከአውሮፓ ሃገር አባርራለሁ ብሎ መዛቱን የቡድኑ መሪ ሚስተር ታይስ በርገን ከሆላንድ ሃገር የዜና አገልግሎት ድርጂት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ተናግረዋል። ዘረኛው መለስ ይህንን የተናገረው የህብረቱን ረቂቅ ቅጂ አስቀድሞ በማንበቡ እንደሆነም ተገልጿል። ሚስተር ታይሰን በዚሁ መግለጫቸው በመላ ሃገሪቱ የሚገኙ የገዢው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ሳይቀሩ ቡድናቸውን ጨምሮ የውጭ ሃገር ዜጎችን ስራ በማጣጣል እንደተዘባበቱባቸው (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች ቡድን የግንቦት 15ቱ ምርጫ አለማቀፋዊ መስፈርቶችን አላሟላም ሲል ገለጸ

ማክሰኞ፣ ግንቦት 16 ቀን የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች ቡድን መሪ አቶ በርማን ለጋዜጠኞች በሰጡት እና ተከትሎም በወጣው የጽሁፍ መግለጫ፣ ቡድኑ የእሁድ እለቱ ምርጫ አለማቀፋዊ መስፈርቶችን እንዳላሟላ መታዘቡን ይፋ አድርጓል።

አቶ በርማን ምርጫው ፍትሃዊ ባልሆነ እና ለገዢው ፓርቲ በሚያደላ ሜዳ ላይ መካሄዱን ገልጸዋል። በመንግስት እና በገዢው ፓርቲ መካከል ልዩነት እንደሌለ እና ገዢው ፓርቲም የመንግስትን ንብረት ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ለምረጡኝ ዘመቻው ሲጠቀም መቆየቱን እንደተመለከቱም ተናግረዋል። . . .

## ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

በተያያዘ ዜና የአልጀዚራ ቴሌቪዥን ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ምንጮቹን ጠቅሶ እንደገለጸው፣ መለስ ዜናዊ የታዛቢ ቡድኑን መሪ ሰኞ እለት በመጥራት ቡድኑን ከአገር ሊያስወጣ እንደሚችል በመናገር ማስፈራራቱን ዘግቧል። አቶ በርማንም ደች ናሽናል ኒውስ ኤጀንሲ ከተባለ የዜና አውታር ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ ቡድናቸው ማስፈራራት እየተደረገበት መሆኑን እንደገለጹ ኢትዮጋርዲያን የተባለው የዜና ድረ-ገጽ ዘግቧል። በተጨማሪም፥ የወያኔው ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማእከል ማክሰኞ ግንቦት 16 ጠዋት ላይ አውጥቶ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባስወገደው ጽሁፍ የታዛቢ ቡድኑን፣ አቶ በርማንን እና አገራቸውን ሆላንድን አብጠልጥሏል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወ/ሮ አና ጎሜዝ በዋሺንግተን ዲሲ ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያውያን በጥበብ እና በአንድነት እንዲነሱ መከሩ

የአውሮፓ ፓርላማ አባል እና በ1997ቱ ምርጫ የአውሮፓ ታዛቢዎች ቡድን መሪ የነበሩት ወ/ሮ አና ጎሜዝ በዩናይትድ እስቴትስ መዲና ዋሽንግተን ዲሲ እሁድ እለት ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያውያን በጥበብ እና በአንድነት እንዲነሱ መከሩ።

ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት በተደረገ የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ላይ ባደረጉት በዚህ ንግግር፣ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ዴሞክራሲ፣ የህግ የበላይነትንና ፍትህን ለማስፈን፤ አስቀድመው የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ እንዳለባቸው ተናግረዋል። ይህንንም ለማድረግ ትብብር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

(የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎምዝ ያቀረቡት ንግግር ሙሉ ቃል በገጽ 3 ቀርቧል)

## የአሜሪካ መንግስት የእሁዱን የምርጫ ተውኔት የሚያወግዝ መግለጫ አወጣ

የአሜሪካው ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ አቶ ማይክ ሃመር ማክሰኞ እለት ባሰሙት መግለጫ እሁድ እለት የተካሄደው ምርጫ ተብዬ ነፃና ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ አልተካሄደም ብለዋል።

መግለጫው፥ አለም አቀፍ ታዛቢዎች ምርጫው አለማቀፋዊ መስፈርቶችን አለማሟሉትን መታዘባቸው እና የአሜሪካ ኤምባሲ ምርጫውን ለመታዘብ የሚያስችላቸውን ፍቃድ መከልከላቸው በአሜሪካ መንግስት ዘንድ ስጋት እና ሃዘኔታን መፍጠሩን ገልጿል። የገለልተኛ ታዛቢዎች መወሰን እና በነፃ መገናኛ ብዙሃን ላይ የሚደረገው ጫናም አጅጉን ይረብሻል ብሏል።

የቅድመ ምርጫው ሁኔታ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫን ለማካሄድ የሚመች አልነበረም ያለው መግለጫ፤ አገዛዙ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በማስፈራራት እና በማጥቃት እንቅስቃሴዎቻቸውን እንደገታ፤ ገለልተኛ ሲቪክ ማህበረሰቡ ላይ ቁጥጥሩን በማጥበቅ እና የነፃ መገናኛ ብዙሃንን እንቅስቃሴ በመግታት የፖለቲካ ምህዳሩን የማጥበብ ስራ መስራቱን መስክሯል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ባለስልጣን ጆኒ ካርሰን በዚሁ ቀን በህዝብ ተወካዮች ፊት ቀርበው ባደረጉት ንግግርም ተመሳሳይ መልክት አስተላልፈዋል። ጆኒ ካርሰን ምርጫው አለማቀፋዊ መስፈርቶችን አለማሟላቱ መንግስታቸውን እንዳሳዘነ ተናግረው፤ የአሜሪካ መንግስት በመለስ አገዛዝ ላይ ጫና እንደሚያደርግ፤ ነገር ግን ከአገዛዙ ጋር ያለውን ግንኙነት አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ እንደሚሆን መግለፃቸውን ሬውተርስ የዜና አገልግሎት ዘግቧል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በግዳጅ እና በክፍያ የተሰበሰቡ ሰዎች የድጋፍ ሰልፍ እንዲያደርጉለት አደረገ

ሰኞ፣ ግንቦት 16 ቀን ለዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ድጋፍ በሚሰጥ ሰልፍ ከተሳተፉት ሰዎች ውስጥ ብዙዎቹ በግዳጅ መሰብሰባቸውን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ለዝግጅት ክፍላችን ባደረሰው መረጃ አስታውቋል።

የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ከስፍራው አጠናክሮ በላከው ዘገባ፣ አብዛኞቹ ሰልፈኞች የትና ለምን እንደሚሄዱ ሳያውቁ የተወሰዱ መሆናቸውን ገልጿል። በርካታ ሰልፈኞች ሰኞ እለት በማያውቁት ምክንያት በነጋታው ጠዋት ወደ ቀበሌ እንዲሰበሰቡ በቀበሌ ሹመኞች መታዘዛቸውን፤ በታዘዙት መሰረት ሲሄዱም በአውቶቢሶች ተጭነው ወደ መስቀል አደባባይ መወሰዳቸውን ለዘጋቢያችን ነግረዋል።

በርካታ የቀን ሰራተኞችም በየቀኑ እየተሰባሰቡ ቀጣሪ ከሚጠብቁባቸው ቦታዎች ተሰብስበው መወሰዳቸው ታውቋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ትብብር፣ ትብብር - ጊዜ የማይሽረው ሕዝባዊና አገራዊ ጥሪ!!!

አንዳንዴ "ግርግር" ሌላ ጊዜ ደግሞ "ተውኔት" ተብሎ ሲጠራ የሰነበተው ነገር ተጠናቀቀ። ከዚህ ግርግርና ተውኔት የሚገኘው ጥቅም ከጉዳቱ ያመዝናል ብለው ከልብ አምነው ህይወታቸውን የሰው ወገኖቻችንን መስዋዕትነታቸው ላመኑበት ጉዳይ ነውና እናከብራቸዋለን። በተጨማሪም በወያኔ ህገ-አልባነት አካላቶቻቸውን ያጡ፤ ሰቆቃ የተፈፀመባቸው፤ የተንገላቱና የተዋከቡ ወገኖቻችን በርካቶች ናቸው፤ የእነሱም ህመም ተካፋዮች ነን። ድካማቸው አለቦታው ውሎ ወያኔን "የህጋዊነት" ካባ አጎናጽፎ፤ በይሉኝታ ቢስነት መላውን የፓርላማ ወንበር እንዲቆጣጠር ቢያደርገውም ግለሰቦችና ቡድኖች ላደረጉት ትግል ግን ተገቢውን እውቅና ልንሰጥ ይገባል።

ወያኔ በ1997ዓ.ም ከርቸሞ በዘጋው በር ላይ የትዕቢት ምስማር ቀርቅሮበት እሱ "ሰላማዊ" ብሎ በሚጠራው መንገድ ተጉዘን የትም እንደማንደርስ በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጦልናል። ነፃ ተቋማት በሌሉበት እና ከጅማሮ እስከ ፍፃሜ በወያኔ መሪ ተዋናይነት ከሚተወን የምርጫ ድራማ የሚጠበቀው ይኸው ነበር። ለራሱ ጨዋታ ማሳመሪያነት ሲል እንኳን በአንዳንድ ቦታዎች ራሱ የመረጣቸው ተፎካካሪዎች ፓርላማ እንዲገቡ አለመፍቀዱ ከማስገረሙ በስተቀር ከአጠቃላይ ውጤት አኳያ ምንም ያልተጠበቀ ነገር አልመጣም። ወያኔ የፓርላማ ወንበሮችን ሙሉ በሙሉ ለመያዝ መወሰኑ "ዲሞክራሲ" በተሰኘ ጫወታው ራሱ ምን ያህል የተሰላቸ መሆኑ ያመላክታል። ወያኔ ወደ ለዘመናት በአምልኮቶት ደረጃ ተሸክሞት ወደቆየው አልባኒያዊ ፍጹም አምባገነናዊ ሥርዓት የሚያደርገውን ጉዞ በሙሉ ልብ መቀጠሉን እና ጉዞውንም እያጠናቀቀ እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ ነግሮናል። ከእንዲህ በወያኔ ምንነትና ማንነት ላይ የሚደረግ ውይይት ይኖራል ብለን አናስብም። ወያኔ የአንድ ግለሰብ ፍጹማዊ አገዛዝ ለማስፈን እና ይህንን አገዛዝ ለረዥም ጊዜ ይዞ ለማቆየት ቆርጧል።

### እኛስ?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከእንግዲህ በአገራችን የወደፊት እጣ ፈንታ ያገባናል የምንል ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ቁርጠኛ የጋራ አቋም እንድንይዝ ጥሪውን ያስተላልፋል። ግንቦት 7 የሁለገብ የትግል አማራጭን እንደስልት ሲነድፍ ለሰላማዊ ትግል ቦታ የሚሰጥ መሆኑን፤ ሆኖም ግን ሰላማዊ ትግል ማለት ከወያኔ ፈቃድ ተጠይቆ በምጽዋት የሚከወን እንቅስቃሴ አለመሆኑን ከዚህ በፊት ሰፊ ማብራሪያ ሰጥቶበታል። "ምርጫ 2002" ተብየው ድራማ ያረጋገጠልን ነገር በወያኔ ብቸና ፈቃድ የሚደረግ ሰላማዊ ትግል ወደ ባርነት እንጂ ወደ ነፃነት የማይወስደን መሆኑን ነው።

ስለሆነም "ከምርጫ 2002" ተብየው ድራማ የእብሪት ውጤት ትምህርት ወስደን:-

1. ወያኔን አስወግደን፤ ነፃ ተቋማትን ገንብተን፤ በነፃና ፍትሃዊ የሕዝብ ምርጫ የተመረጠ መንግሥት ሥልጣን የሚይዝበት ሥርዓት መዘርጋት ግቡ ላደረገ ትግል ቆርጠን እንድንነሳ፤
2. ለዚህ ትግል ደግሞ ቢቻል ልዩነቶቻችን ማቻቻል፤ ካልተቻለ ደግሞ በሚያግባቡን የጋራ ጉዳዮች ላይ ከምርና ከልብ ተባብረን በአንድነት እንድንነሳ፤
3. ይህንን የጋራ ትግል የሚያስተባብር አንድ አካል እንዲቋቋም ሁላችንም በጥልቀት እንድናስብበት፤ እና
4. ትግላችን የተለያዩ ስልቶችን የሚጠቀሙ ድርጅቶችንና ግለሰቦን ማስተባበር የሚሻ እና በተለያዩ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ውስጥ የሚደረግ መሆኑ እግምት ውስጥ በማስገባት በከፍተኛ መተማመን እና ጥንቃቄ እንዲመራ ማድረግ የሚቋቋመው አስተባባሪ አካል አንዱ ትኩረት መሆን ይገባዋል እንላለን።

እንግዲህ ጨክኖ ለመጣብን ጠላት መለሳለስ የሚያስከትለውን ጉዳት በዓይናችን ያየነው ነውና መደገም የለበትም። ሁላችንም በኅበረት በመነሳት አገራችንን እና ሕዝባችንን ከአጠቃላይ ውድቀት እንድናድን። ትብብራችንም ውጤታማ እንዲሆን መዋቅራዊ ይዘት እንዲኖረው ለማድረግ እንጣር። የትብብር ጥያቄ ጊዜ የማይሽረው ቢሆንም አሁን ግን አፍጦ መጥቶብናል። መተባበር መቻል ወይም አለመቻላችን የባርነትና የነፃነት ጉዳይ ሆኗል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ተቀናብሮ በኢትዮጵያ የተካሄደው የምርጫ ተውኔት በተጠበቀው መንገድ ተጠናቀቀ

እሁድ፣ ግንቦት 15 ቀን 2002 አመተ ምህረት በወያኔ ተቀናብሮ በኢትዮጵያ የተካሄደው የምርጫ ተውኔት እንደተጠበቀው፣ ከተፃፈለት ድርሰት አንድም ሳይዛነፍ መጠናቀቁ ታወቀ።

ወያኔ የሚቆጣጠራቸውን የመረጃ አውታሮች ሳይጨምር፤ ከተለያዩ ገለልተኛ የዜና አውታሮች፣ ከግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢዎችና ሌሎች የአይን ምስክሮች የተገኙት መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ምርጫ ተብዬው ከኢ-ፍትሃዊነት አልፎ አስቂኝ ክስተት እንደነበረ አሳይተዋል። ውጤቱ ሲገለጽም፣ በርካታ ታዋቂ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች እንዲያሸንፉ እንዳልተፈቀደላቸው ለማወቅ ተችሏል።

በተቃዋሚ ፓርቲ ታዛቢዎች እና እጩዎች ላይ በአገሪቱ ዙሪያ ወከባ፣ እንግልት፣ ድብደባ እና እስር መካሄዱ በሰፊው የተዘገበ ሲሆን፤ የመድረክ ፓርቲ አመራር አባል አቶ ስዬ አብርሃ አጠቃላይ ሁኔታውን "ደም መፋሰስ የቀረው ጦርነት" ብለውታል።

የመድረክ ፓርቲ አመራር አባል ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ አቡጊዳ ለተባለው የዜና ድረ-ገጽ በሰጡት ቃል፣ "በወላይታ በሃዲያ በከንባታ በምእራብ አርሲ እንዲሁም በበርካታ የደቡብ አካባቢዎች ሕዝቡ ከመምረጡ በፊት ተቀደዉ የተሰፉ፣ በአንዳንድ ቦታዎችም የተሞሉ ኮረጆች" እንደነበሩ ገልጸዋል። በሌላ አካባቢዎችም ኮሮጆዎች ሲታጨቁ መታየታቸውን ዘገባዎች አሳይተዋል።

በተንቤን የሚስጥር ድምጽ መስጫው ድንኳን ውስጥ ገብቶ በቴሌቪዥን ካሜራ ከመቀረጽ አንስቶ፤ ወደ ሰማይ እየተኮሱ ህዝቡን እስከማሸበር መደረሱ ታውቋል። በዚሁ ወረዳም የምርጫ ቦርድ ሃላፊዎች የገዢው ፓርቲ ምርጦች መሆናቸው ሳያንስ፣ እነሱ እንኳ ለስራው ባለመታመናቸው የደህንነት አባላት፣ ካድሬዎች እና የታጠቁ ሃይሎች የምርጫ ጣቢያዎችን ተቆጣጥረው መዋላቸው ታውቋል። አንዳንድ የአዲስ አበባ ጣቢያዎችን ጨምሮ፣ ብዙ በአገሪቱ ዙሪያ የሚገኙ ጣቢያዎች ህዝቡን ለማሸበር ሆን ብለው በተቀመጡ የፖሊስ እና የደህንነት ሰዎች ተከበው መዋላቸውን በርካታ ዘገባዎች እና የአይን ምስክሮች ገልጸዋል።

ወያኔ የተቆጣጠራቸው የህዝብ መገናኛ ብዙሃን፣ በምርጫው ተውኔት በርካታ ህዝብ መሳተፉን ሲያትቱ ቢውሉም፣ ከገለልተኛ መገናኛ ብዙሃን እና ከአይን ምስክሮች የተገኙ መረጃዎች አብዛኞቹ የምርጫ ጣቢያዎች በተለያዩ ሰዓታት ውስጥ ወና እንደነበሩ ገልጸዋል።

### ወ/ሮ አና ጎሜዝ በዋሺንግተን ዲሲ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ከፍፍል እና የሃሳብ መለያየት መኖር በዴሞክራሲያዊ አገሮችም ቢሆን የተለመደ እና ሊጠበቅ የሚገባው መሆኑን ገልጸው፤ በአንዳንድ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ግን መተባበር የግድ ነው ብለዋል።

ወ/ሮ አና ጎሜዝ ኢትዮጵያውያን አዲሱ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት ለምን መረዳት እንዳለበት ለማስረዳት በ1997 ምርጫ ወቅት የነበሯቸውን ገጠመኞች በመጥቀስ፤ በዚያን ወቅት ትልቁን ለውጥ ያስገኘው ተቃዋሚዎች መገናኛ ብዙሃንን በተወሰነ ደረጃ መጠቀም መቻላቸው እንደነበር ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜና የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት ተመልካቾች ቁጥር እያሻቀበ እንደሆነ ኢትዮጵያ ዛሬ የተባለው የዜና ድረ-ገጽ ባወጣው ዘገባ አሳይቷል። በአገሪቱ ዙሪያ አማራጭ መረጃ የማግኘት እድል ከፍተኛ ጉጉትን መፍጠሩን ለዝግጅት ክፍላችን የሚደርሱ አስተያየቶች እያሳዩ ሲሆን፤ ሌሎች ምንጮች በየቀኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ የስልክ መልክቶች ለቴሌቪዥን ድርጅቱ እንደሚደርሱ አሳውቀናል።

### የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች ቡድን የግንቦት 15ቱ ምርጫ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የታዛቢው ቡድን ጋዜጣዊ መግለጫ በተሰጠ ጥቂት ሰዓታት ውስጥ የአውሮፓ ህብረት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ሃላፊ ካትሪን አሽተን የምርጫ ተውኔቱን በሚመለከት ኢትዮጵያውያንን "እንኳን ደስ ያላችሁ" ካሉ በኋላ ህብረቱ ከዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ጋር "ለመስራት እና ትስስሩን ለማጠናከር ዝግጁ መሆኑን" እንደገለጹ የአልጀዚራ ጋዜጠኛ በዘገባው ላይ አክሎ ገልጿል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፣ ቁጥር 106 ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም፤

# የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎምዝ በዋሽንግተን ዲስ ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን በተደረ የገንዘብ ማሰባሰብ ዝግጅት ያደረጉት ንግግር ግንቦት 15 2002 ዓ.ም (ክፍል 1)

የተከበራችሁ ወዳጆቼ በመጀመሪያ እዚህ አርፍጄ በመገኘቴ ይቅርታ ልጠይቅ ይገባኛል። የኔ ጥፋት አይደለም። የኢትዮጵያን ህዝብ ገንዘብ መለስ ዜናዊ ለደላላ ኩባንያዎች እንዳሻው እያርከፈከፈ እንደሚያባክነው ብናውቅም፣ እኔንም እንዲሁ በነዚሁ ደላላ ኩባንያዎች አማካኝነት ለመደለል ጥረት ሲያደርግ ቢከርምም ያሁኑን ጉዞዬን መቼም የኮንቲኔንታል አየር መንገድን ጉቦ ከፍሎ እዚህ ዘግይቶ እንዲደርስ እንዳላደረገው እጠረጥራለሁ። የሞከረም አይመስለኝም።

ለማንኛውም ዛሬ እዚህ ከናንተ ጋ ለመገኘት በመቻሌ እጅግ በጣም ደስታ ተሰምቶኛል። ይህ ቀን ለኔ የሃዘንም የደስታም ቀን ነው። መልካም ትውስታዎች እንዳሉኝ ሁሉ በጣም አሳዛኝ ስሜቶችንም በዉስጤ ይቀሰቅስብኛል። በጣም ጥሩ ትውስታዎች አሉኝ ምክንያቱም የዛሬ አምስት አመት በዛሬዋ ቀን ማለትም ግንቦት ሰባት ቀን የ1997ቱ ምርጫ ቀን እሁድ እለት ነበር ትዝ ይለኛል ኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ ሰአት አካባቢ ነው በኢትዮጵያ የሰአት አቆጣጠር ከምሽቱ ሶስት ሰአት አካባቢ የድምጽ መስጠቱ ሒደት እስከዚያ ሰአት ሲካሄድባቸው ከነበሩት ከአንዱ ቀበሌ ወደሌላው እየተሩዋሩዋጥኩ ነበር። በመጨረሻም ከምሽቱ አራት ሰአት ሲሆን ድምጹን ለመስጠት የድምጽ መስጫው ጠረጴዛ አጠገብ ሰልፍ ይዞ በመጠባበቅ ላይ የነበረውን እና በአዲስ አበባ የመጨረሻው ድምጽ ሰጪ የነበረው ሰው በስፍራው ከጥዋቱ አስራ ሁለት ሰአት ጀምሮ እንደተገኘ ነገረኝ። አብሬውም ፎቶ ተነሳሁ እስከ አሁንም ያንን ፎቶ አስቀምጬዋለሁ።

ከምሽቱ አራት ሰአት ተኩል ላይ ሁሉ ህዝቡ የሚያስገርሙ እና በጣም ረጃጅም ሰልፎች ላይ ቆሞ በጉጉት ለመምረጥ በመጠባበቅ ላይ ነበር። በወቅቱም ህዝቡ ድምጹ ወሳኝ እንደሚሆን እምነት ነበረው። አስታውሳለሁ በ አንድ የድምጽ መስጫ ጣቢያ ከቀትር በሁዋላ ወደ ዘጠኝ ሰአት አካባቢ ተገኝቼ መራጩ ህዝብ በጣም በሚያቃጥል ጸሃይ ላይ ስርአት ባለውና ትእግስት በተሞላበት ሁኔታ በነዚያ እጅግ ረጃጅም በሆኑ ሰልፎች መሃከል ተሰልፎ ድምጹን ለመስጠት ተራው እስኪደርስ እየተጠባበቀ ነበር። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ድንገት ሰልፉ መንቀሳቀስ በማቆሙ ምክንያት ጥቂት የመረበሽ ሁኔታ ይታይባቸው ጀመረ። የእኛንም እዚያ መድረስ ሲመለከቱ እኔን “ምን እያደረጋችሁ ነው” ብለው ጠየቁኝ።፡ወዲያውም አከታትለው “ምን እያደረጉ ነው? ድምጻችንን እኮ እየሰረቁ ነው” አሉን። እኛም የተፈጠረውን ነገር ለማወቅ ወደ ውስጥ ገብተን ስለምናጣራ አትጨነቁ ብለናቸው ቦታው ድረስ በመሄድ ስንመለከት ሰልፉን ለጊዜው ከመንቀሳቀስ የገታው መራጮች ጣት ላይ ምልክት ማድረጊያው ቀለም ማለቁ እነደሆነ እናም ተጨማሪ ቀለም እየመጣ እንደሆነ አስተዋልን። አንድ ግን በጣም ግልጽ የሆነ ነገር የነበረው በሽህ የሚቆጠር ህዝብ ገና ድምጹን ለመስጠት ረጃጅም ሰልፍ ሰርቶ እየተጠባበቀ ባለበት በዚያ ሁኔታ የድምጽ መስጫ ሰአት የሚያበቃበት አስራ ሁለት ሰአት በመቃረቡ ተራ ያልደረሳቸው መራጮች ሰአት ደርሱዋል ተብለው እንዳይመለሱ ስጋት ውስጥ ነበሩ።

አስታውሳለሁ በዚያው ሰአት ወደ ምርጫ ቦርድ ሃላፊው ዘንድ ስልክ ደውዬ በጣም ረጃጅም ሰልፎች ላይ ቆሞ የሚጠባበቅ መራጭ በተለያዩ የየድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ሁሉ ባለበት ሁኔታ ሰልፍ ይዞ የቆመው መራጭ በሙሉ የመምረጥ እድል እንዲያገኝ የድምጽ መስጫ ሰአቱ ቢራዘም የተሻለ ነው የሚል ሃሳብ አቀረብኩኝ። ይህው ሃሳብ ተቀባይነት አግኝቶ ወዲያውም ህዝቡ ይህንኑ ዜና በአንድ ሰ አት ጊዜ ውስጥ በሬዲዮ ሰምቶ በቂ የመምረጫ ሰአት በማግኘት ተረጋግቶ ለመምረጥ ችሎአል። እንዳልኩዋችሁም በአዲስ አበባ የመጨረሻ መራጭ የነበረው ሰው ከምሽቱ አራት ሰአት ተኩል ሲሆን ድምጹን ለመስጠት ችሎአል። ለማስታወሻም አብሬው ፎቶግራፍ ተነስቼአለሁ።

ከዚያም ቀጥዬ የድምጽ ቆጠራ ተጀምሮባቸው ከነበሩ አንድ አንድ ጣቢያዎች መሀል ጉዋደኞቻችን ችግር ተፈጥሮበታል ወዳሉን አንድ መርካቶ አካባቢ ወደሚገኝ የምርጫ ጣቢያ አመራሁ። ይኸውም የድምጽ ቆጠራውን በምን አይነት መንገድ ይከናወን በሚል በተነሳ ውዝግብ የከረረ ጭቅጭቅ በመነሳቱ እኛም ወደዚያ የሄድንበት ምክንያት የእኛ በስፍራው መገኘት ምናልባትም ውጥረቱን ማርገብ ይችል ይሆናል በሚል ነበር። እንዳሰብነውም እዚያ ስንደርስ ብዙ ክርክርና ውጥረት ነበር ሆኖም ግን ከብዙ ውይይት በሁዋላ ቆጠራው ሊቀጥል በሚችልበት አሰራር ላይ ውይይት ተደርጎ መግባባት ተፈጠረና ቆጠራው እንዲቀጥል በመደረጉ እኛም ህዝቡ መተማመኑን አረጋግጠን ጣቢያውን ለቀን ወጣን።

ከዚያም በመቀጠል ወጣቶች ከፖሊሶች እና ወታደሮች ጋር ከፍተኛ ፍጥጫ ላይ ናቸው ወደተባለበት ወደሌላ ስፍራ ሄድኩኝ። ይኸው ቀበሌ የሚገኘው ከ አዲስ አበባ ትንሽ ወጣ ያለ ቦታ ነው። በዚያ ቦታ በርካታ ታንኮች ነበሩ። እነዚሁ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ወጣቶችም ድምጻችን በገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች ተሰርቁዋል የሚል ክሳቸውን ያሰሙ ነበር። በጣም ውጥረት የተሞላበት ሁኔታ ስለነበር በቀላሉ ወደ ሌላ ችግር ሊያመራ ይችል ነበር። ነገር ግን ሁሉም ሰው የበለጠ ችግር እንዳይፈጠር በመስጋት እኛም የተፈጠረውን ጉዳይ እናጣራለን ብለን ወጣቶቹን ለማረጋጋት በመቻላችን ሁኔታዎች ተስተካክለው ሂደቱ ቀጥሎአል።

ያን ቀን ወደ መኝታ የሄድኩት ከለሊቱ ዘጠኝ ሰአት ገደማ ነበር። ወዲያውም ጥዋት አንድ ሰ አት ወይ ሁለት ሰአት ገደማ ከእንቅልፌ እነደነቃሁ የስራ ባልደረቦቼ የሰአት እላፊ መታወጁን ነገሩኝ። ወዲያውም የ አዲስ አበባ የምርጫ ውጤት ሁሉንም ወገን እጅግ የአስደነቀ መሆኑን ነገሩኝ። ተቃዋሚውን ያስደነቀ እንዲሁም ገዢውን ፓርቲም። ምክንያቱም ሃያሶስቱም የ አዲስ አ በባ የፓርላማ መቀመጫ በሙሉ ተቃዋሚዎች ስላሸነፉ ነው። ይህ በጣም ከፍተኛ ድል ነው። ነገር ግን ብዙዎች ስለ 1997ቱ ምርጫ ሲናገሩ ይህንን የላቀ ድል አያነሱትም። ይህ ሁኔታ ግን ትልቅ የፖለቲካ ትርጉም ያለው ነው። ማለትም ሕዝቡን ይህ አዲስ አበባ ላይ የታየው ውጤት የ አዲስ አባባ ብቻ ሳይሆን በመላ አገሪቱ የነበረውን አጠቃላይ የህዝቡን ስሜት ያንጸባረቀ ነበር የሚል እምነት እንዲኖረው አድርጎታል።

አዲስ አበባ ላይ ማጭበርበር የማይቻል ጉዳይ ነበር። ምክንያቱም ህዝቡ ድምጹ እንዳይሰረቅ ነቅቶ ይጠባበቅ ስለነበር ገዢው ፓርቲም ሆነ ሌላ ማንኛውም አካል ሊያጭበረብር የሚችልበት መንገድ አልነበረም። ዉጤቱም ወዲያው በየምርጫ ጣቢያው በራፍ ላይ ተለጥፎ ነበር።

በዛች ቅጽበትም ይመስለኛል መለስ ዜናዊ እና ጉዋዶቹ ስለ ህዝቡ ስሜት የነበራቸውን የተሳሳተ ግምገማ የተረዱት። ተቃዋሚው በርካታ አስቸጋሪ በሆነ እና በተዳከመም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የህዝቡን ድጋፍ ለማግኘት ችሎአል።

በዚህ ወቅት ነበር አለም አቀፍ ታዛቢዎች እኛንም የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎችን ጭምር የቆጠራ ሂደቱን እንዳንታዘብ ክልከላ የተደረገብን።

በበርካታ ቦታዎች የድምጽ ቆጠራ ሂደቱ እንዲቋረጥ ተደረገ። የምርጫ ቦርድ እና አካባቢው የሚገኙ የመንግሰት ሹመኞች የድምጽ ቆጠራው በሚቀጥለው ቀን እንደገና እንደሚጀመር ቢናገሩም በሚቀጥለው ቀን ሂደቱን መታዘብና መከታተል ፍጹም አሰቸጋሪ ሆነ። እኛም ጉዳዩ በጣም በጣም አሳሳቢ ሆነብን። ሆኖም ግን ሂደቱ በመቋረጡ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ያለመተማመን በተቃዋሚውና በገዢው ፓርቲ መካከል ስለተፈጠረ እኛ የምናወጣው መግለጫ የበለጠ ችግር እንዳይፈጥር ብንፈልግም በቆጠራው መቋረጥ ግን እጅግ በጣም ተረብሸናል።

አስታውሳለሁ ምርጫው በተኪያሄደ ከሁለተኛው ቀን በሁዋላ ግንቦት ዘጠኝ ቀን 1997 አ.ም ነበር የመጀመሪያውን ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጠንበት ወቅት በጣም ግልጽ ያደረግነው ነገር ቢሮር ምርጫው በአንድ በኩል ትልቅ የሚባል ችግር ሳያጋጥም የተከናወነ መሆኑን በሌላ በኩል ይኼ ሊሆን የቻለው የኢትዮጵያ ህዝብ ድምጹን ለመስጠት በነቂስ በመውጣት ረጃጅም ሰልፎችን ሰርቶ ስርአት በተሞላበት ሁኔታ ሲጠባበቅ ለዴሞክራሲ ያለውን ቁርጠኝነት ለአለም ሁሉ በማሳየት ስልጡንነቱን ያረጋገጠ መሆኑን፣ ገልጸናል። ይህም ምርጫ ከዚህ ቀደም ተደርገዋል ከሚባሉት ለምሳሌ ገና ከቀኑ ስድስት ሰአት ሳይሆን ምርጫው የተጠናቀቀበት የ1992ቱ ምርጫ ጋር ምንም ተመሳሳይነት እንዳልነበረው በንጽጽር ገልጸናል። ነገር ግን ከሁሉም በላይ አሳሳቢው ነገር የምርጫው ሂደት ያልተጠናቀቀ መሆኑንና የምርጫውን ሂደት ተአማኒ ሊያደርገው የሚችለውና የምርጫውን ዉጤት ወሳኝ ምእራፍ የሚያረጋግጠው ዋነኛው ክፍል የሆነው የድምጽ ቆጠራና ድምር ውጤት ገና ያልተጠናቀቀ መሆኑ በጣም አሳሳቢ መሆኑን በግልጽ አሳውቀናል። ታዲያ ይሄንኑ አደጋ በዚያ በመጀመሪያ በሆነው ጋዜጣዊ መግለጫ ወቅት አሳውቄ ነበር። በነገራችሁ ላይ ይህው ጋዜጣዊ መግለጫ ከመሰጠቱ አምስት ደቂቃ አሰቀድሞ አንድ ስልክ ተደወለልኝ። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ነበሩ የደወሉልኝ። እንዲህም አሉኝ ለመሆኑ በጋዜጣዊ መግለጫሽ “ምን ልትዪ ነው”? የሚል ጥያቄ አቀረበልኝ።

እኔም የሰጠሁዋቸው መልስ “ጠቅላይ ሚኒስትር የምለውንማ እንደሚያውቁ እርግጠኛ ነኝ ምክንያቱም በእኛ መደበኛ አሰራር መሰረት አስቀድመን የደረስንበትን ግምገማ የመንግስት ወኪል ሆኖ በየግዜው ከእኔ ጋር በሚነጋገሩት በሚኒስትር በረከት ስምኦን በኩል ሪፖርቱን ከአንድ ሰአት በፊት ልከንልዎታል። በመሆኑም የምንለውን ሊያውቁት ይገባል የሚል እምነት አለኝ። ዞሮ ዞሮ የምለውን ማወቅ ከፈለጉ ልነግርዎት እወዳለሁ የድምጽ ቆጠራውን በተመለከተ እየሆነ ያለው ነገር እጅግ በጣም አሳስቦኛል። የቆጠራው ሂደት ከምርጫ ቦርዱ ቁጥጥር ዉጪ የወጣ መሆኑ አለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች በበርካታ የ አገሪቱ ክፍሎች የቆጠራውን ሂደት እንዳይታዘቡ መታገዳቸው በጣም አሳሳቢ ነው። ይህ መጥፎ ምልክት ነው። ስለዚህ በዚህ አጋጣሚ ላሳስብዎት የምፈልገው ይህ አሳሳቢ ሁኔታ በአስቸኩዋይ እንዲታረም እንዲያደርጉ ነው። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ግን ስለዚህ ምርጫ የሚኖረን ግምገማ ያሳስበናል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የሚያሳዝነው ያ ሁሉ ህዝብ ዴሞክራሲን ለማምጣት ያሳየውን ቁርጠኝነት ከንቱ አድርጎ ያስቀረዋል።

እንደምታውቁት በዚያ ምሽትም ነበር ሚዲያው በነጻነት እንዳይዘግብ የታገደው። ሰአት እላፊውም እንዲሁ ተፈጻሚ ተደረገ። የ ኢትዮጵያን ሄራልድ ጋዜጣም እንዲሁ ኢሃዴግ አሸናፊ ሆኑዋል ብሎ ድሉን ማብሰሩን ቀጠለ። የብሄራዊ ምርጫ ቦርዱ ቆጠራውን መቆጣጠር ተስኖት ባለበት እና አጠቃላይ የምርጫውን ውጤት ባላወቀበት በዚያ ወቅት የሚያስገርመው የሄራልድ ጋዜጣ ይህ የሚለፍፈውን ውጤት ከየት እንዳመጣው ነው። እንዴትስ ውጤቱን ሊያውቅ ቻለ? እኛ የ አውሮጳ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ከምርጫ ቦርዱ የበለጠ የምርጫውን ውጤት ከብዙ ቦታዎች ለመሰብሰብ ችለናል። ይህውም የሆነበት ምክንያት የአውሮጳ ህብረት ታዛቢዎች በሄዱበት የምርጫ ጣቢያዎች . . . (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው

### ከግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 17 2002 ዓ.ም

ውርደት ውርደት ውርደት፤ ማለቂያ የሌለው ውርደት። የሃገር ውርደት፤ የዜጎች ውርደት፤ የሃይማኖት፣ የሽምግልና እና የፍትህ ተቋማት ውርደት። የድህነት፣ የልመና የስደት ውርደት። የታሪክ፣ የባንዲራና የሃገር ውርደት። የወያኔ አምባገነናዊ ዘረኛ አገዛዝ ስልጣን ከያዘበት እለት ጀምሮ ለሃገራችንና ለህዝቧ በገፍ ሲያመርትላቸው የኖረው ውርደትን ብቻ ነው። በወያኔ ዘመን ያልተዋረደና ያልረከሰ የማንነታችን መሰረት የነበረ እሴትና ተቋም አይገኝም። በመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛ አገዛዝ የቆመበት ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ኢትዮጵያውያንን አስተሳሰብ አገዛዙ በዜጎች ላይ ለሚያሳየው ንቀትና ጥላቻ ለሚፈጽማቸው የማዋረድ ድርጊቶች ዋናው ምክንያት ነው።

በምርጫ ስም ሰሞኑን ወያኔ የፈጸመው አስነዋሪ ድርጊት ባለፉት 19 ዓመታት ሲያሳየን የኖረው የንቀትና የውርደት ስልጠናው ከፍተኛው መገለጫ ነው። የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን በኢትዮጵያ ህዝብ የ1997 ምርጫ ታሪካዊ ክንዋኔ እንዲኮራ ሊያደርገው የሚያስችል ምንም ዓይነት ህዝባዊና ሃገራዊ ትስስር የሌለው በመሆኑ በህዝብ ክንዋኔ መርካትን ሳይሆን መከፋትን እንዲመርጥ ሆኗል። ወያኔ ስልጣንን ከህዝብ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ውጭ ለአምስት ዓመታት በጉልበቱ ይዞ በ1997 ምርጫ በድምጹ የቀጣውን ህዝብ ለማዋረድ ያዘጋጀውን ታላቅ ድግስ እነሆ በሰሞኑ የ2002 የፌዝ ምርጫ ይዞ ብቅ አለ።

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የሰሞኑን የወያኔ የምርጫ ለበጣ ወያኔ ሃገሪቱንና ህዝቧን ለማዋረድ ያዘጋጀው ቋሚ መርሃ ግብር ቀጣይ ድርጊት ነው ብሎ ያምናል። የአስመሳዩ ምርጫ ዓላማ ምን ታደርጉኛላችሁ በሚል እብሪት ተሞልቶ የኢትዮጵያ ህዝብ ለሰላሜና ለብልጽግናዬ፣ ለአንድነቴና ለነጻነቴ ዋስትና ይሆናል ብሎ ተሰፋውን በጣለበት የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ህልሙ ላይ በብልግና የተሞላ እጣቢ መድፋት ነው።

ወያኔ ህዝብንና እንድካክርሃለን ያሉትን የፖለቲካ ፓርቲዎች አፍኖ፣ በመደለል በማስፍራራት በመደብደብ በመግደል ያከናወነው የምርጫ ተውኔት ዓላማው ህዝብን መበቀልና ማዋረድ ብቻ ነው። በ1997 ምርጫ ወያኔ አንድ ድምጽ ለማግኘት በተቸገረባቸው ከተሞችና ገጠሮች ራሱን የመቶ በመቶ ድምጽ አሸናፊ እያደረገ፤ በዓለም ላይ በአምባገነን አገዛዞች ስር የተደረጉ የቅጥፈት ምርጫዎችን ሬኮረዶችን ሰበርኩ ሲለን እታመናለሁ ብሎ ሳይሆን “እሱቲ የምትሆኑትን አያለሁ” የሚል በእብሪት የተሞላ ንቀቱን ሲገልጽልን ነው።

ከ547 የምክር ቤት መቀመጫዎች መሃል ለተቃዋሚ አንድ መቀመጫ ሰጥቶ 546ቱን አሸነፍኩ ይህንን ውጤት በጸጋ ያልተቀበለ ልብሱ እየወለቀ ይገረፋል ሲለን ቅስማችሁን ሰብሬ አዋርጄ እገዛችኋለሁ ምንም ልታደርጉ አትችሉም እያለን ነው። እንዲህ አይነቱ አዋራጅ ድርጊት ወያኔ ሲፍጽምብን የመጀመሪያው ባይሆንም ያሁኑ ልዩነቱ የወያኔን አዋራጅ ድርጊት ወደን የገባንበት ለመሆኑ በድምጻችን ያረጋገጥበት ማስረጃ አለኝ ማለቱ ብቻ ነው። የ2002 ምርጫ ወያኔ በደፋው የአምባገነንነት ዘውድ ላይ ተራራ የሚያክል የእብሪት ፈርጥ ከመጫን ሌላ ትርጉም የለውም።

የወያኔ የማጭበርበር ምርጫ ያስነሳው አቧራ ሲጠራ ኢትዮጵያውያን ከፊታችን ቆሞ ያገኘነው አንድ ጥያቄ ብቻ ነው። “እንደ ሃገር፣ እንደ ህዝብና እንደ ሰብአዊ ፍጥረት ይህንን አዋራጅ ስርዓት እስከ መቼ ተሸክመን መቀጠል እንችላለን?” የሚለው ነው። በእንዲህ አይነቱ ውርደት ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች የሚኖሩባት ሃገር እውን ሃገር መባል ትችላለችን፤ ነዋሪዎቿስ ዜጎች ተብለው መጠራት ይቻላሉን? ለመሆኑ እስከመቼ ነው ይህንን አዋራጅ ስርዓት እንዲቀጥል የምንፈቅድለት?

ዛሬ በመለስ ዜናዊ አማካይነት በሁላችንም ላይ የተጫነው ውርደት በፖለቲካ አመለካከትና በምንከተለው የትግል ስልት ልዩነት ልናድበስብሰው ከማንችልበት ደረጃ በላይ ተሸጋግሯል። የቋንቋ፣ የባህልና የእምነት ልዩነቶቻችንን እንቅፋት ሳይሆኑብን በጋራ ልንመክተው የሚገባ የመንፈስ ቁስል ሆኗል። ወቅቱ እያንዳንዱ ዜጋ እራሱን የሚመረምርበት፣ “እንዴት ራሴን፣ ቤተሰቤን፣ ማህበረሰቤንና ሃገሬን ለእንዲህ ዓይነቱ ውርደት አበቃሁ?” ብሎ ራሱን የሚጠይቅበት ወቅት ነው።

ወቅቱ ስብራታችንን የምናሽበት፤ ለራሳችንም የምናዝንበት ሊሆን አይገባም። ቅጥረኞች ለሚያኪያሂዱት ቅስም ሰባሪ ፕሮፓጋንዳ ጆሮዋችንን የምንከፍትበት ጊዜ ሊሆን አይገባም። ይልቁንስ ወቅቱ በወያኔ ማንነትና ምንነት ላይ የጋራ ግንዛቤ ይዘን በጋራ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ምስረታ የምንነሳበት ነው። ከማንኛውም ነገር በላይ በወያኔ የተገፈፈውን ሰብዓዊ ክብራችንን ለማስመለስ “ውርደት በቃን” የምንልበት ነው።

ወያኔ ሰሞኑን በምርጫ ስም የፈጸመው ነውር የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የጀመረውን ትግል ፍትሃዊነትና የሚከተለው ሁለገብ የትግል ስልት ትክክለኛነትን አረጋግጧል። እምቢ ለዘረኛወና አምባገነኑ ወያኔ በሚል እልህ ከሁሉም ሃገራችን የዴሞክራሲ ሃይሎች ጋር ተባብረን ወያኔን ከማስውገድ ውጭ በሃገራችን ዴሞክራሲን ማስፈን እንደማንችል አመላክቶናል።

የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ: “የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!” የሚል ነው።

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

## የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎምዝ በዋሽንግተን ዲሲ ያደረጉት ንግግር ሙሉ ቃል

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የታዘቡትን እና በየምርጫ ጣቢያዎቹ ደጃፍ ላይ ከተለጠፈው ውጤት ባገኘነው መረጃ መሰረት ነው።

ከዘጠኝ ቀናት በሁዋላ ተጨማሪ መግለጫ አወጣን። በዚህ መግለጫችን አሁንም በድጋሚ የምርጫ ቦርዱ የምርጫውን ዉጤት ሊቆጣጠር ያለመቻሉን ገለጽን። እኛ የሰበሰብነው የምርጫ ውጤት ከምርጫ ቦርዱ ካሰባሰበው የበለጠ መሆኑን እናም በዚያ ግዜ ምን እየተደረገ እንዳለ ሁላችንም እናውቃለን። መንግስት ቆጠራውን አስተጉዋጉሎ ድምጽ የመስረቁን ስራ ተያይዞት ነበር። ይህንንም ማድረግ ያስፈለገው አዲስ አበባ ላይ ህዝቡ ለተቃዋሚዎች ድምጹን በመስጠት 23ቱንም መቀመጫ ተቃዋሚዎች እንዲወስዱ በማድረግ ሽንፈት ስላከናነቡት ያንን ማካካሻ መሆኑ ነበር ማጭበርበሩ።

እንግዲህ የቀረውን ታሪክ ሁሉ የምታውቁት ነው። የአውሮጳ ህብረት ታዛቢ ቡድን ይፋ ያልሆነውን ሪፖርቱን ህዝብ ጋ እንዲደርስ ሆን ብሎ አፈትልኮ እንዲወጣ አድርጉዋል የሚል ክስ ተናፈሰ። እኔ በበኩሌ እስከዛሬዋ ቀን ድረስ ያን የተባለውን ሪፖረት ማን እንዳወጣው አላውቅም ። ይህ እንዲሆንም ያደረገውን ሰው ለምን እንደተደረገም አላውቅም። ሆኖም ግን በሁኔታው ተጸጽቻለሁ። ምክንያቱም ያ የተባለው ሪፖርት እኛ በግንቦት 16 ቀን በሰጠነው መግለጫ ላይ ካካተትነው መረጃ የበለጠ የተሻለ መረጃ አልነበረውም። ሆኖም ግን አስታውሳለሁ ሰኔ አንድ እና ሁለት በአዲስ አበባ በተደረገው ጭፍጨፋ እለት አንድ በጭፍጨፋው የተገደሉ ሰዎች አስከሬኖች እና ቁስለኞች እየተቀበለ የነበረ ሆስፒታል ሁኔታውን ለመመልከት ሄጄ ነበር። እዚያም ስደርስ መቼም ቢሆን ፊታቸው ላይ የነበረው ሃዘን የማይረሳኝ ነርሶችና ዶክተሮች በህዝቡ ላይ በደረሰው የግፍ ጭፍጨፋ ተማረው እና እነዚህን ወገኖች ከሞት ሊታደጉዋቸው ባለመቻላቸው ፍጹም ተስፋ ቆርጠው እየተቆጩ ነበር። ከዚያም እንደተመለስኩ በቀጥታ ከቀኑ ወደ ስምንት ሰአት ገደማ ይሆናል ስለጭፍጨፋው እና ስለተመለከትኩት ነገር የተሰማኝን ልነግረው ወደ ሚኒስቴር በረከት ስምኦን ቢሮ አመራሁ። በወቅቱም ወደ እሱ ቢሮ ላየው በሄድኩ ወቅት ፍጹም በሃዘን በተዋጠ ስሜት ውስጥ ነበርኩ። (ክፍል 2 በሚቀጠለው ሳምንት ይቀርባል)

## በርካታ የተቃዋሚ ፓርቲዎችና የአውሮፓ ህብረት . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

ተናግረዋል። በምርጫው ወቅት ተከሰቱ ስለተባሉት ችግሮች የተጠየቁት በርማን ምርጫው ተቃዋሚዎችን በማግለል ለገዢው ፓርቲ ባደላ መልኩ እንደተካሄደ ጠቅሰዋል። የገዢው ፓርቲ በምርጫ ዘመቻ ወቅት የብዙሃን መገናኛን በብቸኝነት ተገልግሎበታል ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ የመንግስት ንብረቶችን ለፓርቲ አገልግሎት አውሏል የሚሉትን ነጥቦች ሚስተር በርማን በምሳሌነት ጠቅሰዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ሚስተር በርማን የታዛቢዉ ቡድን ያወጣዉን ሪፖርት «የኢትዮጵያ ህዝብ ማወቅ ይኖርበታል» በሚል ያለ ምንም መሸራረፍ ይፋ ይደረግ ዘንድ ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት በጻፉት ደብዳቤ ገልጸዋል። ሚስተር በርማን በዚሁ ደብዳቤ ፤ ኢትዮጵያን ሄራልድ የተሰኘዉ ጋዜጣ በዛሬዉ እትሙ የአዉሮፓ ሕብረት ያወጣዉ ሪፖርት በተመለከተ ባሰፈረዉ ጽሁፍ፤ በሪፖርቱ ያሉትን ጥሩ ጥሩ ጎኖች ብቻ በማዉጣት ፤ በሪፖርቱ የሰፈሩ በጣም ጠቃሚ ትችቶች አለመግለጻቸዉ እንዳሳዘናቸዉ ገለጸዋል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በግዳጅ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

ዘጋቢያችን ካናገራቸው ብዙዎችም ለተሳትፏቸው እንደሚከፈላቸው አረጋግጠዋል።

ተመሳሳይ ሰልፎች በሌሎች ከተሞችም የተካሄዱ ሲሆን፤ በአዲስ አበባው ሰልፍ ላይ መለስ ዜናዊ እራሱ ተገኝቶ ንግግር አድርጓል። የሰልፉ ርእስ “ድምፃችን ይከበር” የሚል ሲሆን፤ ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለውን አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ቡድን እና ምእራባውያንንም አውግዟል።

በረከት ስምኦን ለምርጫው ሰሞን የህዝብ ግንኙነት መመሪያ ማውጣቱን ባለፈው ሳምንት የዘገብን ሲሆን፤ ከተዘረዘሩት ተግባራት አንዱ ህዝቡ ሰላማዊ ሰልፎችን በመውጣት ለአገዛዙ ድጋፍ እንዲያሳይ ማድረግን ያካትታል።

## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ
## የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

## ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org